## ትምህርት 4

## ኃጢአት በሰው ዘር ላይ የሚያስከትላቸው ውጤቶች/መዘዞች፣ ዘፍ 3፡16-19

እግዚአብሔር የፈጠራቸው አዳምና ሔዋን አዘጋጅቶ ባስቀመጣቸው የኤደን አትክልት ስፍራ አትብሉ ካላቸው የአንድ ዛፍ ፍሬ ባይበሉ ኖሮ ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው ያማረ ህብረት ሳይበላሽ በሰላም፣ በእረፍት፣ በደስታ፣ ጥቂት በመስራት ብዙ ምርት እያገኙ የተመቻቸ ኑሮ በመኖር ይቀጥሉ ነበር፡፡ ነገር ግን ኃጢአት በማድረጋቸው ሁኔታው ተለዋወጠ፡፡

ኃጢአት በሰው ዘር ሁለንተናዊ ሕይወት ካስከተላቸው አስከፊ ችግሮች ዋነኞቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

1. **ብርሃንን ያጠፋል**፡- *ማለትም አእምሮን ያጨልማል፤ መንፈሳዊ ነገሮችን የመረዳት አቅም እየቀነሰ እንዲሄድና እንዲጠፋ ያደርጋል፤ እያደር ልብን ያደነድናል/ያጠነክራል፡- ሰው ኃጢአት በማድረግ ሲቀጥል የእግዚአብሔር ትእዛዛት ለመጣስ የባሰ ደፋር እየሆነ ይሄዳል፤ ህሊናን ያደነዝዛል፡- ህሊና ሃጢአት የሆነውና ያልሆነውን ነገር የሚያመዛዝን/የሚለይ ሃጢአት ሲሰሩ ተጸጽተው እንዲመለሱ የሚያደርግ የሰው ውስጣዊ ሰውነት አንዱ ክፍል ነው፡፡ ሰው ኃጢአት በማድረግ ሲጸና የህሊና ጸጸትም እየጠፋና እየደበዘዘ ኃጢአት መውደድ እያየለ ይሄዳል፡፡*
2. **ከእግዚአብሔር ጋር ይለያያል/ጥለኛ ያደርጋል** (ኢሳ 59፡1-2)፡- *ሰው ኃጢአት በማድረግ እየጸና ሲሄድ ኃጢአት ከሚጠላው እግዚአብሔር ጋር አንድ የሚያደርገው ወይም የሚያመሳስለውና ህብረት እንዲኖረው የሚያደርግ ባህርይ እየተለወጠ፣ የሚያስማማው ነገር እየጠፋ ይሄዳል፡፡ ለምሳሌ ያህል የእግዚአብሔር ባሕሪያት ፍቅር፣ ትግስት፣ ይቅር ባይነት ሲሆን የሰው ባህሪ ጥላቻ፣ ቁጡ፣ ቂመኛ ከሆነ የሰውዬውና የእግዚአብሔር ባህርያት ምንም ተመሳሳይነት /አንድንት/ የሌላቸው ተቃራኒዎች ሆነዋል ማለት ነው፡፡ የሰው ባህሪ እግዚአብሔር ከሚወደው ባህሪ ተቃራኒ እየሆነ ሲቀጥል ሰው የእግዚአብሔር ጠላት ይሆናል ማለት ነው፡፡*
   *ከዚህም የተነሳ የእግዚአብሔርን ማዳን፣ ጥበቃ፤ ቸርነት፣ ባርኮት … ከኃጢአተኛው ሰው ያርቃል ወይም ያጎድላል፣ በችግር ጊዜ ወደ አግዚአብሔር ቢጸልዩም እርዳታ እንዳይገኝ ያደርጋል፣ ሰላም፣ ደስታና ውስጣዊ ዕረፍት ያሳጣል፣ ሁከት፣ ፍርሃትና ጭንቀትን ያስከትላል፡፡ እግዚአብሔርም በተለያየ መንገድና ሁኔታ ኃጢአተኛን ይቀጣል፡፡ ነገር ግን ሰው እግዚአብሔር የሚወደው ባህሪ/ተግባር እየተለማመደና እየጨመረ ሲሄድ ወደ እግዚአብሔር ይበልጥ እየተጠጋ ይቀርባል፣ እግዚአብሔርም አብሮት ይሆናል ወይም ኅብረት ይኖረዋል፡፡ ከእግዚአብሔርም የሚያስፈልገውን በረከት ያገኛል፡፡*

3. **ለተለያዩ ቁሳዊና መንፈሳዊ ጠላቶች ተገዥነት/ባርነትና ተሸናፊነት ይዳርጋል፡፡**
   *ሀ. አውቆ/ወዶ ኃጢአት ማድረግ፣ በኃጢአት ላይ ኃጢአት እየጨመሩ መሄድ* ***ለኃጢአት ባርነት*** *ይዳርጋል፡፡ ይህም ማለት ኃጢአት ሊላቀቁት የማይቻል ልማድ ወይም እንደ ከባድ ሱስ ኃይል ይኖረዋል ማለት ነው፡፡ ዮሐ 8፡34* ***"ኃጢአት የሚያደርግ የኃጢአት ባሪያ ነው፣"*** *የሚለው ለዚህ ነው፡፡ (ኤር 13፡23፤ መክ 8፡8 ያንብቡ)*
   ***ለ. ከህግ እርግማን በታች ያደርጋል***
   *ዘዳ 28፡15-68 ባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እግዚአብሔር እስራኤላዊያንን ኃጢአት ካደረጉና በኃጢአታቸው እየቀጠሉ ከሄዱ ምን ዓይነት ከባድ የሆኑ ችግሮች በሕይወታቸውና*

በልጆቻቸው ላይ እንደሚደርስባቸው ዘርዝሮ ነግሯቸዋል፡፡ እነዚያ ከእግዚአብሔር በኃጢአታቸው ምክንያት የሚያገኛቸው ቅጣቶች ዕርግማን ተብለው ተጠርተዋል፡፡

በምድራዊ ሕይወት የተለያዩ ችግሮች እንዲደርሱ ያደርጋል፡

- በተለያዩ የሰው፣ የእንስሳትና የእጸዋት ጤንነት ጎጂ በሽታዎችና ችግሮች መሰቃየት፤
- በተለያዩ የተፈጥሮ አደጋዎች መጠቃት፡- ድርቅ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ ወይም የመሬት መናድ፣ ከባድ ዝናብ፣ ብዙ ሕይወት፣ ሃብትና ንብረት የሚያጠፋ ጎርፍ፤ በከባድ አውሎ ነፋስ መጠቃት፤
- በጦርነት ሰርተው ያገኙት በረከት ሁሉ መውደም፣ መዘረፍ፣ በስደት መንገላታት፣ ሰላማዊ ሰው ሳይቀር በጭፍጨፋ መሞት፤
- በምድራዊ ኑሮ ራስን ለመቻል ዕለት ተዕለት የሚሰሩት ስራ (የእርባታ፣ የእርሻ፣ የንግድ፣ የሙያና የጉልበት … ስራ) ፍሬያማ/ስኬታማ አለመሆን፤
- የወለዱት ዘር አለመባረክ፣
- በአእምራዊ በረከት አለመባረክ፤

**ሐ. ለጠላት ተሸናፊነት ይዳርጋል፡- ለሰይጣንና ለክፉ መናፍስት/ለባዕድ አማልክት፣ ለወራሪ አገራት ተገዥነት** ይዳርጋል፡፡ ኃጢአት በማድረግ ጸንቶ መቀጠል ከእግዚአብሔር ጋር ተጣልቶ/በእግዚአብሔር አምጾ መራቅ/መኮብለል/መሸፈት ማለት ነው፡፡ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ከሌለው የእግዚአብሔር ጥበቃም አይኖረውም፡፡ ስለዚህ ክፉ መንፈስ ሲያጠቃው ብቻውን መቋቋም ስለማይችል ተሸንፎ ተገዥ/ተጠቂ ይሆናል፡፡ ይህች ምድር በሁለት በዓይን በማይታዩ መንግስታት (ገገሮች) ትገዛለች፡፡ እነርሱም የእግዚአብሔር መንግስትና የሰይጣንና አጋንንቱ መንግስት ናቸው፡፡ የእግዚአብሔር መንግስት የሚገዛው ምድርን ብቻ ሳይሆን፣ በሰማየ ሰማያት ያሉት ወሰን አልባ ብዛት ያለላቸው ፍጥረታትን ሁሉ ነው፡፡ አንድ ሰው በፈቃደኝነት በእግዚአብሔር ቃልና በመንፈስ ቅዱስ ምሪት መሰረት በመታዘዝ በቅድስና በመኖር ፈንታ የራሱን ፈቃድና ምኞት በመከተል ኃጢአት በማድረግ ጸንቶ የሚቀጥል ከሆነ ይህ ሰው ከአግዚአብሔር መንግስት ኮብልሎ ለሰይጣንና አጋንንቱ መንግስት እጁን የሰጠ ወይም የጨለማው ዓለም ተገገር የሆነ ሰው ነው ማለት እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል፡፡ (ዮሐ 8፡41፣ 44፣ 1ዮሐ 3፡8ን ይመልከቱ፡፡)

ስለዚህ ማንኛውም ሰው ወይ ለእግዚአብሔር መንግስት ይገዛል፤ ወይ ደግሞ ለሰይጣንና አጋንንቱ ተገገር ይሆናል እንጂ እንዲሁ መሀል ሰፋሪ ወይም ገለልተኛ ሆኖ መኖር አይችልም (የለም)፡፡ እግዚአብሔር በራሳቸው ምርጫ ወደውና ፈቅደው ያለ ማንም አስገዳጅነት የሚያምኑትን፣ የሚታዘዙትና የሚያመልኩትን ይፈልጋል፣ ይቀበላል፣ ከሰይጣንና አጋንነቱ ጥቃትም ይጠብቃል፡፡ ሰይጣን ግን ማንኛውም እግዚአብሔርን መከተል ያልፈለገና የእግዚአብሔር ጥበቃ የሌለውን ሰው ፈቀደም አልፈቀደ በማሳትና በማስገደድ ጭምር በቁጥጥሩ ስር ያደርጋል፡፡

**መ. ለዘላለም ሞት ፍርድ ይዳርጋል**፤ - ማንኛውም ኃጢአት በማድረግ ቀጥሎ ከእ/ር የራቀ ሰው በምድራዊ ኑሮው ከሚደርስበት መርገምና የጠላት ጭቆና በተጨማሪ የዘላለም ሕይወት በማጣት የመጨረሻውና ከሁሉም ከባድ ወደሆነው በእግዚአብሔር የፍርድ ቀን ወደ ገሀነም እሳት እንደሚጣል መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል፡፡

ይህ ሲባል ግን በአሁኑ ዘመን የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርጉ ቅዱሳን በምድራዊ ኑሯቸው ምንም ችግር አይደርስባቸውም ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን በኃጢአተኛ ላይ በሚመጣ ቅጣት፣ በሚነግሱ መንፈሳዊ ጠላቶችና የዘላለም ሞት ተጠቂ/ተገዢ እንዳይሆኑ እግዚአብሔር ይጠብቃቸዋል (ይዋጋላቸዋል)፡፡ ማስረጃ የሚሆኑ ጥቅሶች እነዚህ ናቸው፡፡

**ሮሜ** 6፥23፣ "የኀጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር ስጦታ ግን በጌታችን በክርስቶስ ኢየሱስ የዘላለም ሕይወት ነው።"
**ዕብራውያን** 9፥27 "ሰው አንድ ጊዜ ሊሞት ከዚያም በኋላ በፍርድ ፊት ሊቆም ተወስኖበታል።"
**2ኛ ቆሮንቶስ** 5፥10 "ሁላችንም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት እንቀርባለንና፤ እያንዳንዱም ሰው በሥጋው ለሠራው በጎ ወይም ክፉ ሥራ ተገቢውን ዋጋ ይቀበላል።"

ማንኛውም ሰው የኃጢአት ምንነትና ኃጢአት በሚያደርገው በማንኛውም ሰው ላይ የሚያስከትለው እጅግ አስከፊ ውጤት ካላወቀ እግዚአብሔርንም አይፈራም፣ እግዚአብሔርም ኃጢአት ከሚያስከትልበት መራራ ጽዋ ከመጨለጥ የሚያድነው ብቸኛ መፍትሔ ጌታ ኢየሱስን ቢያቀርብለትም አሜን ብሎ አይቀበልም፡፡ ይህም የሚያደርገው ምንም ኃጢአት ቢሰራ ማንም የማያውቀበትና የሚያስከትልበት መዘዝ ያለ ስለማይመስለው ነው፡፡